# ፩ኛ ክፍል

# የሙዚቃ ሲለበስ

# ክፍለ ትምህርት አንድ፡- የሙዚቃ ምንነት መገለጫዎቹና ጠቀሜታ / 7 ክፍለ ጊዜ/

ተማሪዎች ዓላማ፡- ተማሪዎች ይህን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ

- የሙዚቃ መገለጫዎችና አጠቃቀምን ያውቃሉ፣
- ሙዚቃ ለሌሎች ትምህርቶች የሚሰጠውን ድጋፍ ይገነዘባሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | 1. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ/ 1 ክፍለ ጊዜ/ | |
| ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ<br>▪ የሙዚቃ ድምፅ ምድቦችን ይገልፃሉ፣ | 1.1 የድምፅ ምድብ<br>▪ ሙዚቃዊ ድምፅ (Musical Sound)<br>▪ ሁካታ (Noise) | ▪ ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድ ተነስተው ከአሁን በፊት የተማሩትን ስለድምፅ ምድብ እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>▪ በተማሪዎች ሀሳብ መነሻነት ስለድምፅ ምድብ ገለፃ መስጠት፣ |
| ▪ የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ /ዳይናሚክስ/ መገለጫዎችን ምልክታቸውን ከነጠቀሜታቸው ይዘረዝራሉ፣<br>▪ ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ግንኙነትና ድጋፍ ሰጪነት ያስረዳሉ፣ | 1.2 የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ መገለጫ ቃል ምልክቶች/ዳይናሚክስ/<br>▪ ፎርቴ /f /<br>▪ ፒያኖ /p/<br>▪ ፎርቲሲም/ ff /<br>▪ ፒያኖሲም / pp<br>/2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው ስለ ሙዚቃ ጥዑመ ለዛ መገለጫ ምልክቶች፣ አጠቃቀም ላይ እንዲወያዩና በተግባር እንደሞክሩ ምሳሌዎች በመስጠት መርዳት፣<br>▪ ጥዑመ ለዛዎቹን በተለያየ መንገድ እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>▪ በሙዚቃ መሣሪያ<br>▪ በመዝመሮች |
| | 1.3 ሙዚቃ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ግንኙነትና ድጋፍ ስጪነት | ▪ ከመዋዕለ ሕፃናት ት/ቤትና ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ባለሙያ በመጋበዝ ወይም |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | ▪ በመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት<br>▪ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት<br>/1 ክፍለ ጊዜ/<br><br>1.4 መዝሙር የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ መዝሙር<br>▪ ስለሙዚቃ ጠቀሜታ የሚያንፀባርቅ መዝሙር /3 ክፍለ ጊዜ/ | የጉብኝት ኘሮግራም በመንደፍ ሙዚቃ ለሕፃናት ትምህርት የሚሰጠውን ድጋፍ እንዲገነዘቡ በማድረግ ሪፖርት እንዲያጠናቅሩ ማበረታት፣<br>▪ ተማሪዎች የአጠናቀሩትን ሪፖርት በየተራ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>▪ ስለኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ምንነትና አስፈላጊነት ማብራሪያ በመስጠት አመቺ መዝሙር የማስተማር ዘዴን በመጠቀም ማዘመር፣ |

**ክትትልና ግምገማ ፡-**

- የድምፅ ምድብን መዘርዘራቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ ምልክቶችን ተጠቅመው መዝሙሮችን መዘመራቸውን ወይም ቀላል የሙዚቃ መሣሪያዎችን በምልክታ ማረጋገጥ፣
- ሙዚቃ ለሌሎች ትምህርቶች የሚሰጠውን ድጋፍ ማብራራታቸውን በጥያቄዎች ማረጋገጥ፣

**ማስተማሪያ መሣሪዎች፡-**

- ቴኘሪኮደር መዝሙር የተቀረጸባቸው ካሴቶች በቻርት የተዘጋጀ የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ መገለጫዎች ወዘተ..፣ ቀላል የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች፣

## ክፍል ትምህርት ሁለት፡- የሙዚቃ ቴዮሪ /18 ክፍለ ጊዜ/

አጠቃላይ ዓላማ፡- ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- የሙዚቃ ኖታዎች አከፋፈል ፅንሰ ሀሳብን ያውቃሉ፣
- የሙዚቃ ድምፆችን በስታፍ ላይ መፃፍንና ማንበብን ይችላሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| 1. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ / 1 ክፍለ ጊዜ/ | | |
| ተማሪዎች ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ<br>▪ የጊዜ ቆይታን የሚያመለክቱ ኖታዎች አከፋፈል ፅንሰ ሀሳብን ያስረዳሉ፣<br>▪ ከሙሉ ኖታ እስከ 1/8ኛ ያሉ ኖታዎችን ከነእረፍት ጊዜ ምልክቶቻቸው በቅርፅና በጊዜ ቆይታ መጠናቸው ይለያሉ፣ | 1.1 የኖታዎች የጊዜ ቆይታ<br>▪ ሙሉ ኖታ<br>▪ ግማሽ ኖታ / ½ /<br>▪ ሩብ ኖታ/ ¼ /<br>▪ 1/8 ኖታ ከነእረፍት ጊዜ ምልክቶቻቸው | ▪ ስለኖታዎችና የእረፍት ጊዜ ምልክቶች ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>▪ ከተማሪዎች አስተያየት በመነሳት ከሙሉ ኖታ እስከ 1/8 ኖታ ድረስ ቅርፃቸውንና አጠቃቀማቸውን በዝርዝር ማስረዳት፣<br>▪ የኖታዎችና የእረፍት ምልክቶቻቸው ቻርት፣ ፍላሽ ካርዶች በመጠቀም ተማሪዎች የበለጠ እንዲለዩዋቸው ማድረግ፣ |
| ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት/3 ክፍለ ጊዜ / | | |
| ▪ በጂ ክሌፍና በኤፍ ክሌፍ ስታፍ የመሥመሮችንና የክፍት ቦታዎችን ስም ይለያሉ፣<br>▪ ኤፍ ክሌፍን በስታፍ ላይ ትክክለኛውን ቦታ ላይ ያስቀምጣሉ፣<br>▪ ሁለት ረዳት መሥመሮችን በመጠቀም ከስታፍ በላይና በታች ኖታዎችን | 1.2 የሙዚቃን ድምፅን በስታፍ ላይ መፃፍ<br>▪ ጂ ክሌፍ ስታፍ<br>▪ ኤፍ ክሌፍ ስታፍ<br>▪ የረዳት መሥመሮች (ledger lines) አጠቃቀም | ▪ ተማሪዎች በተለያየ መንገድ ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶቻቸውን በማፃፍ ማለማመድ፣<br>▪ በቅድሚያ ተማሪዎች ስለስታፍና ክሌፍ የሚያውቁትን እንዲገልፁ ማድረግ፣<br>▪ ከተማሪዎች ሀሳብ በመነሳት የኤፍ ክሌፍ አሠራር፣ በስታፍ ላይ የሚኖረውን ትክክለኛ ቦታ ሠርቶ ማሳየት፣<br>▪ የኤፍ ክሌፍ አሠራርና በስታፍ ላይ ያለውን |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
| --- | --- | --- |
| አስፋፍተው ይፅፋሉ፣ | | አቀማመጥ ተማሪዎች እየሠሩ እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>▪ የረዳት መሥመሮችን አጠቃቀም በተደጋጋሚ ሠርቶ በማሳየት ተማሪዎችን ማለማመድ፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በመከፈል በኤፍ ክሌፍ የስታፍ መሥመሮችና ክፍት ቦታዎች ስያሜን እንዲሁም የረዳት መሥመሮች አጠቃቀም ላይ ተወያይተው ያገኙትን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያስረዱ ማድረግ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የኖታ አከፋፈል ስልቶችን መረዳታቸውን ሠርተው እንዲያሳዩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፣
- ከሙሉ ኖታ እስከ አንድ ስምንተኛ ኖታ ከእነእረፍት ምልክቶቻቸው ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣
- በኤፍ ክሌፍ ስታፍ የመሥመሮችና ክፍት ቦታዎችን ስሞች መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- የረዳት መሥመሮችን አጠቃቀም በፅሑፍ እንዲሠሩ በማድረግ በምልከታ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-**

- የኖታዎችን አከስፈል የሚያሳይ ቻርት
- የኖታ ቻርቶች የኖታ ፍላሽ ካርዶች፣
- የረዳት መሥመሮችን አጠቃቀም የሚያሳይ ቻርቶች ወዘተ…

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| **3. ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሦስት/ 1 ክፍለ ጊዜ /** | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑሳን ክፍለ ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፡-<br>▪ የአጋጣሚ ምልክቶችን(accidental gins) ይዘረዝራሉ፣<br>▪ የአጋጣሚ ምልክቶች የሚሰጡትን ትእዛዝ ይለያሉ፣ | 3.1 የአጋጣሚ ምልክቶች (accidental Signs)<br>▪ ሻርፕ /#/<br>▪ ፍላት /b/<br>▪ ናቹራል /♮/ | ▪ ተማሪዎች ስለአጋጣሚ ምልክቶች የሚያውቁትን እንዲናገሩ እድል መስጠት፣<br>▪ የአጋጣሚ ምልክቶች ምንነት፣ ዓይነትን በሙዚቃ ውስጥ የያላቸውን ሚና አስመልክቶ ገለፃ ማድረግ፣<br>▪ የሙዚቃ ድምፆችን በተናጠል በመውሰድ የአጋጣሚ ምልክቶችን አነባበብ በምሳሌዎች ደጋግሞ ማሳየት፣<br>▪ ተማሪዎች የሙዚቃ ድምፆችን በአጋጣሚ ምልክቶች እንዲያነቡና እንዲፅፉ ማለማመድ፣<br>▪ |
| **4 ንዑስ ክፍለ ትምህርት አራት/ 3 ክፍለ ጊዜ /** | | |
| ▪ የቀላል የጊዜ አመልካቾችን አጠቃቀም ይገልፃሉ፣<br>▪ በቀላል የጊዜ አመልካች የተፃፉ ኖታዎችን ያነባሉ፣<br>▪ የቁልፍ ድምፅ አመልካችን ምንነትን ያብራራሉ፣<br><br>▪ የሚያንፀባርቁ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br>▪ ከመዝሙሩ ጋር የተያያዙ ፅንሰ ሀሳቦችን ይገነዘባሉ፣ | 4.1 የጊዜ አመልካች (Time signature)<br>▪ ቀላል የጊዜ አመልካች 2 3 4 / 4 4 4<br>▪ የቁልፍ ድምፅ አመልካች (Key Signature)<br><br>4.2 መዝሙር የዲሞክራሲ መርሆዎችና እሴቶችን የሚያፀባርቅ መዝመር /1/ /2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ የጊዜ አመልካች ምንነትን ከሚያውቁት ተነስተው እንዲናገሩ ማበረታታት፣<br>▪ በቀላል የጊዜ አመልካች የተፃፉ ቦታዎችን በመጠቀም አጠቃቀሙን ደጋግሞ ማሳየት፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል በተለያዩ የጊዜ አመልካቾች ኖታዎችን ሠርተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ ማድረግ፣<br><br>▪ የቁልፍ ድምፅ አመልካች ምንነትና ጠቀሜታ በምሳሌዎች በዝርዝር ማስረዳት፣<br>▪ የመዝሙር ቃላት በማስጠናት አመቺ በሆነ የመዝሙር ማስተማር ዘዴ በመጠቀም ማዘመር፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የአጋጣሚ ምልክቶችን ዓይነትና የሚሰጡትን ትእዛዝ መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- የቀላል የጊዜ አመልካችን ምንነትና ጠቀሜታ እንዲያስረዱ መጠየቅ፣
- በቀላል የጊዜ አመልካች የተፃፉ ኖታዎችን ማንበባቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- መዝሙሩን በትክክል መዘመራቸውን በምልክታ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-**

- በይዘቶቹ ላይ የተዘጋጁ ቻርቶች ፍላሽ ካርዶች
- ኪ ቦርድ የተገኘ ማንኛውም የዘመናዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | 5. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አምስት/2 ክፍለ ጊዜ / | |
| ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ፡-<br>▪ የሻርፕና ፍላት ሜጀር ስኬል አደራደር ሥርዓትን ይለያሉ፣<br>▪ ሜጀር ስኬሎችን በፊደለት አማካኝነት ደርድረው ያሳያሉ፣ | 5.1 **የሜጀር ስኬሎች አደራደር**<br>▪ ሻርፕ ሜጀር ስኬል C.G.D<br>▪ ፍላት ሜጀር ስኬል F $B^b$ $E^b$ | ▪ ተማሪዎች ስለ ስኬል ያላቸውን ግንዛቤ በቅድሚያ እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>▪ የሻርፕ ሜጀር ስኬል አደራደር ስልትን ሠርቶ በማሳየት ደጋግሞ ማስረዳት፣<br>▪ የፍላት ሜጀር ስኬል ከሻርፕ ሜጀር ስኬል አደራደር የሚለይበትን ሥርዓት ሠርቶ በማሳየት ማስረዳት፣<br>▪ እንደአመቺነቱ በግልና በቡድን ተማሪዎች የሻርፕ ሜጀር ስኬልን የፍላት ሜጀር ስኬሎችን በፊደላት እያፃፉ እንዲለማመዱ ማድረግ፣ |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ፡-<br>▪ የባቲ ቅኝቶች አደራደር ሥርዓትን ያስረዳሉ፣ | 5.2 ባህላዊ /ጥንታዊ / የባቲ ቅኝት<br>▪ ባቲ ቅኝት መነሻ ሲናጂ /2 ክፍለ ጊዜ /<br>5.3 መዝሙሮች / 2 ክፍለ ጊዜ /<br>▪ በባቲ ቅኝት የተደረሱ መዝሙሮችን /ዘፈኖች/ | ▪ ስለባህላዊ ቅኝት የሚያውቁትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ መጠየት፣<br>▪ በባቲ ቅኝት የተደረሱ ዘፈኖችን ማሰማት፣<br>▪ የትዝታ ቅኝት አደራደር ላይ ክለሳ በማድረግ የባቲ ቅኝት አደራደርን ማስረዳት፣ |
| ▪ የባቲ ቅኝትን ከሲና ጂ በመነሳት በፊደላት ደርድረው ያሳያሉ፣<br>▪ የትዝታ ቅኝትንና የባቲ ቅኝትን አንድነትና ልዩነት ይዘረዝራሉ፣ | 5.4 በባቲ ቅኝት የተደረሱ ዘፈኖችን ማድመጥ፣ | ▪ የትዝታ ቅኝትና የባቲ ቅኝት አደራደርን በማነፃፀር በፊደል በመደርደር ማስረዳት፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የትዝታ ቅኝትና የባቲ ቅኝት አንድነትና ልዩነት ላይ ተወያይተው የደረሱበትን በቡድን ተጠሪዎች በኩል ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ▪ በባቲ ቅኝት የተደረሱ መዝሙሮችን ወይም ዘፈኖችን ይዘምራሉ፣<br>▪ የመዝሙሩ የሚያስተላልፈውን መልእክት ያስረዳሉ፣ | | ▪ በቡድኖች ሥራዎች ላይ ክፍሉን በማወያየት አጠቃላይ ማብራሪያ መስጠት፣<br>▪ በተመረጡ መዝሙር የማስተማር ዘዴ ተጠቅሞ መዝመሩን ማስጠናት፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የሻርኘ ሜጀር ስኬል የፍላት ሜጀ ስኬል አደራደር ሥርዓትን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ተከታታይ ሜጀር ስኬሎች በፊደላት መደርደር መቻላቸውን ሠርተው እንዲያሳዩ በማድረግ ማረጋገጥ፣
- የትዝታና ባቲ ቅኝት አደራደርን እንዲያስረዱ መጠየት፣

**ማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** - ቴፕሬኮርደር በመዝሙር የተቀረፀበት ካሴት

- ኪ-ቦርድ /ከተገኘ/ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡- ሶልፌጆ (Solfeggio) /8 ክፍል ጊዜ /

**አጠቃላይ አለማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከጠናቀቁ በኋላ፡-

- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ያሉ ኖታዎችን ከእነ እረፍት ምልክቶቻቸው ማንበብ ይችላሉ፣
- የሙዚቃ ድምፆችን ከቀላል ምቶች ጋር በማቀናጀት መዘመር ይችላሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| 3. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ /2 ክፍለ ጊዜ / | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ<br>▪ ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎችና፣የእረፍት ምልክቶቻቸውን ያነባሉ፣<br>▪ ኖታዎቹንና የእረፍት ምልከቶቻውን አድምጠው ይጽፋሉ፣<br>▪ በቀላል ሪትሞች የተጻፉ ዜማዎችን አድምጠው ይዘምራሉ፣ | 3.1 ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎችና የእረፍት ምልክቶቻቸው የንባብ ልምምድ<br>3.2 ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎች ከነእረፍት ምልክቶቻቸው በማድመጥ የመጻፍ ልምምድ /1 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ ካሁን በፊት ስለሚያውቁት የሙዚቃ ምልክቶች ኖታዎች አነባብ በማስታወስ እንዲያስረዱ ጥያቄ በማቅረብ ማበረታታት፣<br>▪ የሙዚቃ ኖታዎችና የእረፍት ምልክቶች የአነባብ ስልቶች በቅደም ተከተል ማስረዳት፣<br>▪ ምሳሌዎችን ደጋግሞ በመስጠት አነባቡን ማሳየትና ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማድረግ፣<br>▪ ሪትሞችን እንዴት ስምተው እንደሚጫወቱ ዘዴውን ማሳየት፣<br>▪ አጨዋወቱን ምሳሌ በመስጠት ማሳየት፣<br>▪ የተለያዩ መልመጃዎችን በግልና በቡድን እንዲጫወቱ በመስጠት ትምህርቱን ማጠናከር፣ |
| ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት | | |
| ▪ በቀላል ምትና ዜማ የተጻፉትን የሙዚቃ ድምፆች ከዶ-ሶል ከእስታፍ ላይ አይተው ይዘምራሉ፣ | 3.3 ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎች በቀላል ሪትሞች የተጻፉ ዜማዎች አድምጦ መዝመር፣ /2 ክፍለ ጊዜ / | ▪ ከሙሉ እስከ ሩብ ኖታዎች በቀላል ሪትሞች የተጻፉ ዜማዎችን በማስማት ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ▪ የመንገድ ደህንነት የሚያንፀባርቅ መዝሙር ይዘምራሉ፣ | 3.4 በቀላል ምትና ዜማ የተጻፉትን የሙዚቃ ድምፆች ዶሬሚፋሳል ከእስታፍ ላይ አይቶ መዘመር / 1 ክፍለ ጊዜ / | ▪ በቀላል ምትና ዜማ የተዘጋጁ የሙዚቃ ድምፆች ከእስታፍ ላይ አይተው እንዴት እንደሚያነቡ ማሳየት ቀላል መልመጃዎችን መስጠት፣ |
| ▪ መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን መልእክት ያስረዳሉ፣ | 3.5 የመንገድ ደህንነት የሚያንፀባርቅ መዝሙር /1 መዝሙር/ / 2 ክፍለ ጊዜ | ▪ ለመዝሙሩ ተስማሚ የሆነውን መዝሙር የማስተማር ዘዴዎችን በመምረጥ ማለማመድ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ምልክቶቻቸው እንዲያነቡ በማድረግ መከታተል፣
- ኖታዎችና የእረፍት ምልክቶችን አድምጠው መጻፋቸውን በተግባር ማረጋገጥ፣
- በቀላል ሪትሞች የተጻፉ የሙዚቃ ድምፆችን ከእስታፍ ላይ አይተው መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-**

- ቴፕሪከርደር፣ በካሴት የተቀረጹ መዝሙሮች፣ ከበሮ፣ ሪትምክስቲክ፣ ኖታዎችን የያዙ ፍላሽ ካርዶች
- ከተገኘ ኪ ቦርድ ግሎክን ሽፒል ወዘተ…

## ክፍለ ትምህርት አራት፡- ሙዚቃን ማድመጥ / 6 ክፍለ ጊዜ/

### አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ሙዚቃን የመድመጥና የአዳማመጥ ሥርዓትን ያዳብራሉ፣
- የብሔር ብሔረሰብን ሙዚቃዎች በማድመጥ የማድነቅ ክህሎታቸውን ያደብራሉ፣
- ዘመናዊ ሙዚቃን በማድመጥ የመሣሪያዎችን አይነት ያውቃሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| 4. ንዑስ ክፍል ትምህርት አንድ /1 ክፍለ ጊዜ/ | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማሩ በኋላ<br>▪ ሙዚቃን የማድመጥና የአዳማመጥ ሥርዓትን ይለያሉ፣<br><br>▪ ተከታታይ የሙዚቃ ድምፆችንና አክታብን ይለያሉ፣<br>▪ የብሔር ብሔረሰቦችን ሙዚቃ በማድመጥ ለይተው ይናገራሉ፣<br><br>▪ ኤች አይቪን መከላከልና የኤድስ በሽተኞችን እንክብካቤ የሚገልጹ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br>▪ መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን መልእክት ያስረዳሉ፣<br>▪ በሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ ዜማዎችን በማድመጥ የመሣሪያዎቹን | 4.1 ተከታታይ ድምፆችንና ኦክታቭ መለየት<br><br><br>4.2 የብሔር ብሔረሰቦችን ሙዚቃዎች ማድመጥ /1 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ ካሁን በፊት ስለሚያውቁት የሙዚቃን የአዳማመጥ ሥርዓትን እንዲያስረዱ ማድረግ፣<br>▪ ዋና ዋና የአደማመጥ ሥርዓቶችን ማብራራት<br>▪ ተቀራራቢ ተከታታይ ድምፆችንና አክታብን ምን እንደሆኑ እንዲረዱ ማድረግ፣<br>▪ ተቀራራቢ ድምፆችን አክታብንማስማት፣<br>▪ በካሴት የተቀረጹ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃዎችን እንዲያዳምጡ ማድረግ ስላዳመጡት የብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃ እንዲናገሩ እድል መስጠት፣<br><br>▪ ለመዝሙሩ ተሰማሚ የሆነውን መዝሙር የማስተማር ዘዴን በመምረጥ ትምህርቱን ተግባራዊ ማድረግ፣<br>▪ በዘመናዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ ዜማዎችን ማስደመጥ፣ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ዓይነት ይዘረዝራሉ፣ | 4.3 ከኤች አይቪ ኤድስ/መከላከልና የኤድስ ሕሙማንን ከመንከባከብ ጋር የተያያዘ መዝሙር /ዘፈን/ / 2 ክፍለ ጊዜ/<br>4.4 በዘመናዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ የተለያዩ ሙዚቃዎችን ማድመጥ / 2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ ሙዚቃዎቹን ካዳመጡ በኋላ በውስጡ ያሉትን የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት ምን እንዲሆኑ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>▪ ከቡድን ውይይት በኋላ ያዳመጡትን የሙዚቃ መሣሪያዎች አይነት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- ዋና ዋና የአደማመጥ ሥርዓቶችን መለየታቸውን ጥያቄዎችን በማቅረብ ማረጋገጥ፣
- የአደመጡት የብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃን እንዲናገሩ በማድረግ፣
- የአዳመጡት ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ስም መዘርዘራቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- የኤች አይቪ ኤድስ መዝሙር መዘመራቸውን ጥያቄ በማቅረብ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-**

- ቴፕሪከደር፣ የብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃዎችን የያዙ ካሴቶች፣ በዘመናዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ ዘፈኖችን የያዘ ካሴት ወዘተ…

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡- የሙዚቃ ታሪክ /8 ክፍለ ጊዜያት

ለአጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ

- ታዋቂ የሀገር አቀፍ የሙዚቃ ባለሙያዎችን ታሪክና ሥራዎቻቸውን ያውቃሉ፣
- የዘመነ ክላስካል ታዋቂ ደራሲያን ታሪክና ሥራዎች ያውቃሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| **2. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ ሀገር አቀፍ ሙዚቃ/2 ክፍለ ጊዜ/** | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ፡-<br>▪ የያሬድን ታሪክ ሥራዎች ያስረዳሉ፣<br>▪ የያሬድ የዜማ ስልቶችን ይለያሉ፣<br>▪ የያሬድን የዜማ ምልክቶችን ይዘረዝራሉ፣ | 2.1 ጥንታዊ ሙዚቃ በኢትዮጵያ<br>▪ የያሬድ ታሪክና ሥራዎች /505-671 ዓ.ም/ | ▪ ተማሪዎች ስለ ያሬድ ታሪክና ሥራዎች የሚያውቁትን በየተራ እንዲናገሩ ማበረታታት፣<br>▪ የያሬድን ታሪክ በትረካ፣ በንባብ ወዘተ… ለተማሪዎች ማስረዳት፣<br>▪ የያሬድ የዜማ ስልቶችንና የዜማ ምልክቶቹን ዓይነት ማስረዳት፣ |
| **2.2 ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት/ 1 ክፍለ ጊዜ/** | | |
| ▪ በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ የተመሠረበትን ዘመን ይገልፃሉ፣<br>▪ በየዘመናቱ ለሙዚቃ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከቱ የሙዚቃ ሙያተኞችን ይዘረዝራሉ፣ | 2.2.1 የታላላቅ ሀገር አቀፍ የሙዚቃ ባለሙያዎች ታሪክና ሥራዎቻቸው<br>▪ በዘመናዊ ሙዚቃ አጀማመርና እድገት ያበረከቱት አስተዋፅዖ ቅድመ ጣሊያን ወረራ /1887-1927 ዓ.ም /<br>▪ 1887-1916<br>▪ 1916-1927<br>▪ 1933-1966 | ▪ ተማሪዎች በቡድን በመከፋፈል በያሬድ ታሪክ በያሬድ የዜማ ስልቶችና በያሬድ የዜማ ምልክቶች ላይ ተወያይተው ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ መርዳት፣<br>▪ ቡድኖች ያዘጋጁትን በየተራ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>▪ ተማሪዎች ስለቡድኖቹ አቀራረብ አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>▪ ከተማሪዎች አቀራረብ በመነሳት የማጠናከሪያ ገለፃ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ▪ የሥነ ምግባር መርሆዎችና እሴቶች የሚገልፁ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣ ከመዝሙሩ የሚያገኙትን ፍሬሃሳብ ይገልፃሉ፣ | 2.3 መዝሙር የሥነ ምግባር መርሆዎችና እሴቶችን የሚያንፀባርቅ /2 ክፍለ ጊዜ/ | ማድረግ፣<br>▪ የዘመናዊ ሙዚቃ ምንነት ተማሪዎች ከሚያውቁት በመነሳት እንዲናገሩ መጋበዝ፣<br>▪ በትምህርቱ ይዘት ላይ በተቀመጡት የዘመናት ምድብ የነበሩ ሥራዎችና ከፍተኛ አስተዋፃዖ ያበረከቱ ሙያተኞችን ታሪክና ሥራዎች ማብራራት፣<br>▪ እንደአመቺነቱ ባለሙያ በመጋበዝ ውይይት ማካሄድ፣፡<br>▪ ከባለሙያ የቀረቡትን ፍሬ ሀሳቦች በማጠናከር ማብራሪያ መስጠት፣<br>▪ የመዝሙር ማስተማር ዘዴ ተጠቅሞ ማዘመር፣ |

**ክትትልና ግምገማ**

- የያሬድን ታሪክና ሥራዎቹን እንዲያብራሩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፣
- ስለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ አደማመጥ እድገት እንዲያስረዱ መጠየቅ፣
- ታዋቂ ሀገር አቀፍ የሙዚቃ ሙያተኞችን ስምና ሥራዎቻቸውን እንዲገልፁ መጠየቅ፣
- የሥነ ምግባር መርሆዎችና እሴቶች የሚያንፀባርቀውን መዝሙር መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** ምስሎች ፎቶግራፎች የያሬዳዊ ምልክቶች ቻርት ቴፕሪከርደር ካሴት፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| **3. ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሦስት ዓለም አቀፍ/3 ክፍለ ጊዜ/** | | |
| ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ፡-<br>▪ የክላሲካል ሙዚቃ ዘመንን ይገልፃሉ፣<br>▪ በዘመነ ክላሲካል ታዋቂ የነበሩ ደራሲያን ሦስቱን በስም ይለያሉ፣<br>▪ የክላሲካል ሙዚቃ ደራሲያኑን የሕይወት ታሪክና ሥራዎች ይዘረዝራሉ፣<br>▪ ከደረሲያኑ በጣም ቀላልና ማራኪ የሆኑትን ዜማ በመስጠት ያደንቃሉ፣<br><br>▪ በምግብ ራስን ከመቻል /ልማት/ ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br><br>▪ በምግብ ራስን መቻል አስፈላጊነትና ጠቀሜታን ይገነዘባሉ፣ | 3.1 የዘመነ ክላሲክ ታዋቂ ሙዚቃ ደራሲያን ታሪክና ሥራዎች፣<br>▪ ሞዛርት<br>▪ ቬትሆቨን<br>▪ ጁሴፔ በርዲ<br>/1 ክፍለ ጊዜ/<br>3.2 የሞዛርት፣ ቤትሆቨንና ጁሴፔ ቨርዲ ታዋቂ ሙዚቃዎች፣<br><br>3.3 መዝሙር፡- በምግብ ራስን ከመቻል/ልማት/ ጋር የተያያዙ መዝሙር /ዘፈን/፣<br>/2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ ተማሪዎች ስለሙዚቃ ታሪክ የሚያውቁትን በቅድሚያ እንዲናገሩ እድል መስጠት፣<br>▪ ቅድመ ክላሲካል ዘመንን በአጭሩ በመግለፅ የክላሲካል ዘመን መቼ እንደነበር፣ የሙዚቃ ድርሰት ዓይነቶችን ታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያንን ታሪክና ዋና ዋና ሥራዎች ላይ ገለፃ ማድረግ፣<br>▪ እነዚህን ደራሲያን ታዋቂ ሥራዎች እንዲያዳምጡ ማድረግና ካዳመጡ በኋላ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ እያንዳንዱ ቡድን ስለክላሲካል ዘመን ሙዚቃ ባህርያትን ስለታዋቂ የሙዚቃ ደራሲያንን ታሪክና ሥራዎች ባለሙያዎችን በማነጋገር ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣<br><br>▪ በቡድን ያዘጋጁትን ሥራዎች በክፍል ውስጥ በየተራ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>▪ በቀረበው የቡድን ሥራዎች ላይ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>▪ የተማሪዎችን ሀሳብ በማሰባሰብ ጥሩ ዝግጅት ያቀረቡትን ቡድኖች በማድነቅ ሌሎችም ለወደፊቱ በተመሳሳይ እንዲሠሩ ማበረታታት፣<br>▪ እንደመዝሙሩ ክብደትና ቅለት ተስማሚ የመዝሙር ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ ማዘመር፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የክላሲካል ዘመንን እንዲገልፁ መጠየቅ፣
- ከዘመኑ ክላሲካል የታወቁ ሙዚቃ ደራሲያንን ሥራዎች እንዲተርኩ ማድረግ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-**

- የክላሲካል ሙዚቃ ደራሲያንን ምስሎች ፎቶግራፎች
- ቴፕሪኮርደር፣ ሙዝሙሩ የተቀረጸበት ካሴት
- በክላሲካል ሙዚቃ የታወቁ ደራያንን የሙዚቃ ዱርሰቶች የያዙ ቪዲዮ ካሴቶች፣
- ቪዲዮ ሪኮርደር፣

# ክፍል ትምህርት ስድስት፡- ባህላዊ ሙዚቃዎች/18 ክፍለ ጊዜ/

ለአጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የአካባቢያቸውን ባህዊ ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎችን በመሰብሰብ መተንተን ይችላሉ፣
- ባህላዊ ሙዚቃዎቹንና ዳንኪራዎቹን ከድርጊቶች ጋር በማቀናጀት መጫወት ይችላሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| 6. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ/ 4 ክፍለ ጊዜ/ | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑሳን ክፍለ ትምህርቶች ከተማሩ በኋላ፡-<br>▪ ከአካባቢው ሥነ ውበት፣ ሥነ ምግባር እንስሳትና አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችና ዳንኪራዎች ጋር የተያያዙ ዘፈኖችን ይሰበሰባሉ፣<br>▪ የዘፈኖቹን ግጥምና ዜማ አጨዋወት የሚያጅቡ የሙዚቃ መሣሪያዎችና አልባሳት ዘፈኖቹ የሚቀርቡበት ጊዜ ቦታ አጨዋወት ይተነትናሉ፣ | 6.1 ባህላዊ ሙዚቃዎች /ባህላዊ ዘፈኖችና ንኪራዎች/መሰብሰብ፣<br>▪ የአካባቢ ውበትን የሚያንፀባርቅ<br>▪ ሥነ ምግባርን የሚያንፀባርቅ<br>▪ እንስሳትን የሚያንፀባርቅ<br>▪ አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ<br><br>6.2 ባህላዊ ሙዚቃዎችን መተንተን<br>▪ ግጥምና ዜማ<br>▪ ዘፈኖቹን የሚያጅቡ የሙዚቃ መሣሣሪያዎች<br>▪ አልባሳት<br>▪ ዘፈኖች የሚቀርቡበት ጊዜ ቦታ አጨዋወት /2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ የንዑስ ክፍለ ትምህርቱ ዓላማና ይዘት የሚያክናወኑትን ዋና ዋና ተግባራት በማስተዋወቅ እንዲወያዩበትና አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>▪ በአካባቢያቸው ስለሚያውቋት ውበትን፣ ሥነ ምግባርን እንስሳትንና አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችን ዳንኪራዎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>▪ የዘረዘሩዋቸውን ባህላዊ ዜማዎችና ዳንኪራዎች እንዲሰበስቡ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የአሰባሰቡን ቅደም ተከተልና መመሪያ ማስረዳት፣<br>▪ በቡድን የሰበሰቡዋቸውን ሥነ ውበትን፣ ሥነ ምግባርን እንስሳትንና አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችንና ዳንኪራዎችን ከራሳቸው ልምድ በመነሳት እንዲያስረዱ ማድረግ<br>▪ የሰበሰቡትን በህላዊ ዜማዎችና ዳንኪራዎች የመተንተኛ መስፈርት እንዲያዘጋጁ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ▪ ከተፈጥሮን የማድነቅ ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br>▪ መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን ፍሬ ሐሳብ ይገልጻሉ፣ | 6.3 ተፈጥሮን ከማድነቅ ጋር የተያያዘ መዝሙሮች /2 ክፍለ ጊዜ/ | ሀ/ የዘፈኖቹ ግልጽ ትርጉም ለምሳሌ ውበትን የሚያንባርቀ ምን ማለት እንደሆነ<br>ለ/ የዘፈኖቹ ግጥምና ዜማ፣ መች ማን እንደደረሳቸው<br>ሐ/ የአጨዋወት ስልት ጊዜና ቦታ ወዘተ... በግልፅ ማስቀመጥ፣<br>▪ ዘፈኖቹ በመስፈርቱ መሠረት እንዴት እንደሚተንትኑት ማስረዳት፣<br>▪ የዘፈኖቹን ትንተና በቡድን ሆነው ተራ በተራ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>▪ በቀረበው ላይ የክፍሉ ተማሪዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>▪ ለመዝሙሩ ተስማሚ የሆነውን የመዝሙር ማስተማር ዘዴዎችን በመምረጥ ተግባራዊ ማድረግ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-** - በአካባቢያቸው ውበትን፣ ሥነ ምግባርን፣ እንስሳትን፣ አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችን መሰብሰባቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

- የዘፈኖቹን ግጥም ዜማ አጨዋወት፣ ዘፈኖቹ የሚቀርቡበትን ጊዜና ቦታ ሲተነትኑ በማየት ማረጋገጥ፣ ተፈጥሮን የማድነቅ
- መዝሙር መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡** - ቴፕሪከርደር፣

- ባህላዊ ዘፈኖቹ የተቀረፁባቸው ካሴቶች፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ንዑስ ክፍል ትምህርት ሁለት/7ክፍል ጊዜ/ | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑሳን ክፍል ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-<br>▪ የአካባቢያቸው ሥነ ውበትን፣ ሥነ ምግባርን እንስሳትንና አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችና ዳንኪራዎችን ይጫወታሉ፣ | 6.4 ባህላዊ ዘፈኖችን ከድርጊቶችና ከሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በማቀናጀት መጫወት፣<br>▪ የአካባቢ ሥነ ውበትን<br>▪ ሥነ ምግባርን<br>▪ እንስሳትንና<br>▪ አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችና ዲኪራዎች፣<br>▪ ዘፈኖቹን የሚያጅቡ የሙዚቃ መሣሪያዎች | ▪ ተማሪዎች ካሁን በፊት በአካባቢያቸው ስለሚያውቁት የአካባቢ ሥነ ውበት፣ ሥነ ምርግባር፣ እንስሳትን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዘፈኖችና ዳንኪራዎች ውይይት ካደረጉ በኋላ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲገልጹ እድል መሰጠት፣<br>▪ የተማሪዎችን ሐሳብ መነሻ በማድረግ ስለ ባህላዊ ዜማዎቹና ዳንኪራዎች ማብራሪያ መስጠት፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ በመጀመሪያ ባህላዊ ዜማዎቹን በመቀበል ከዳንኪራዎቹ ጋር እንዲለማመዱዋቸው ማድረግ። በ ልምምዱ ወቅት ሞደል የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ሌሎች ተማሪዎችን እንዲያለማምዱና እርስበራሳቸው እንዲረዳዱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ማበረታታት፣<br>▪ ባህላዊ ዘፈኖቹንና ዳንኪራዎቹን ከተለማመዱ በኋላ ከሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር ለማለማመድ መሣሪያዎቹን መጫወት የሚችሉ ተማሪዎች ካሉ በየቡድኑ አሰባጥሮ መመደብና እነዚህ ተማሪዎች እንዲያሳዩና እንዲያለማምዱ ማድረግ፣ |
| ▪ ዘፈኖቹን ከቀላል የሙዚቃ መሣሪያዎችና ድርጊቶች ጋር አቀናጅተው ይጫወታሉ፣<br>▪ ስለ ጥቁሮች የነፃነት ተጋድሎ የሚያወሳ መዝሙር ይዘምራሉ፣ | 6.5 ከጥቁሮች የነፃነት ተጋድሎ ጋር የተያያዘ መዝሙር /የእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተደረሱ መዝሙሮች/<br>/ 3 ክፍል ጊዜ/ | ▪ አንድም ተማሪ መሣሪያዎቹን የሚጫወት ከሌለ ከተቻለ በአካባቢው መሣሪያዎቹን የሚጫወቱ ሰዎችን ወደ ት/ቤት በመጋበዝ እንዲያሳዩዋቸው ማድረግ፣<br>▪ ተማሪዎቹ የተመለከቱትን እንዲለማዱ ማድረግ፣<br>▪ ከልምምዱ በኋላ ቡድኖቹ ሥራዎቻቸውን ለክፍሉ ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲያቀርቡ በማድረግ ማበረታታት፣<br>▪ በቀረበው የቡድን ሥራ ላይ የክፍሉ ተማሪዎች አስተያየታቸውን |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ▪ መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን ፍሬ ሐሳብ ያስረዳሉ፣ | | እንዲያቀርቡና እርስ በራሳቸው እንዲማማሩ ማድረግ፣<br>▪ እንደ መዝሙሩ ቅለትና ክብደት ተስማሚውን መዝሙር የማስተማር ዘዴዎችን በመምረጥ መዝሙሩን ማለማመድ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የአካባቢያቸው ውበትን፣ ሥነ ምግባርን፣ እንስሳትንና አዕዋፍን የሚያንፀባርቁ ባህላዊ ዜማዎችና ዳንኪራዎች መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የጥቁሮች የነፃነት ተጋድሎ የሚያወሱ መዝሙሮች/ዘፈኖች/ በቡድንና በግል መዘመራቸውን ጥያቄ በማቅረብ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** ቴፕሪኮርደር ባህላዊ ዜማዎች የተቀረጹባቸው ካሴቶች በአካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ቀላል የሙዚቃ መሣሪያዎች፣

## ክፍል ትምህርት ሰባት፡- የሙዚቃ መሣሪያዎች/6 ክፍል ጊዜ/

አጠቃላይ ዓላማዎች ተማሪዎች፡-

ይህንን ክፍል ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ዋና ዋናዎቹን የክልሉንና ሀገር አቀፍ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነትና አጠቃቀም ያውቃሉ፣
- ዓለም አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ዓይነት ያውቃሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| 7. ንዑስ ክፍል ትምህርት አንድ/ 1ክፍል ጊዜ/ | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑሳን ክፍል ትምህርቶች ከተማሩ በኋላ፡-<br>▪ የክልሉን የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት ይዘረዝራሉ፣<br><br>▪ የሙዚቃ መሣሪያዎቹ አጠቃቀም ያስረዳሉ፣<br><br>▪ አገር አቀፍ የተንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ዓይነት ይዘረዝራሉ። የመሣሪያዎቹን አጠቃቀም ያስረዳሉ፣ | 7.1 የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች ምድብ<br><br>7.2 የክልል የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነትና አጠቃቀም /1 ክፍል ጊዜ/<br><br>7.3 ሀገር አቀፍ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነትና አጠቃቀም<br>▪ ዋሽንት<br>▪ እምቢልታ<br>▪ መለከት ወዘተ... | ▪ ተማሪዎች በክልላቸው የሚያውቁትን የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነትና አጠቃቀም በቡድን ከተወያዩባቸው በኋላ የደረሱበትን ፍሬ ሐሳብ ለክፍላቸው ተማሪዎች በዝርዝር እንዲያቀርቡ ማበረታታት፣<br>▪ የተማሪዎቹን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ የክልሉን የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች አይነትና አጠቃቀም ማብራራት፣<br>▪ የክልሉን የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሞዴሎችን በማሳየት አጠቃቀሙን እንዲያስረዱ ማድረግ፣<br>▪ ስለ ሀገር አቀፍ የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች የሚያውቁትን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ማድረግ፣<br>▪ የተማሪዎቹን ሐሳብ መነሻ በማድረግ ስለአገር አቀፍ የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪየዎች ዓይነትና አጠቃቀም በተለይ በዋሽንት፣ እምቢታና መለከት ላይ ትኩረት በማድረግ ማብራሪያ መስጠት፡ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ▪ ዋና ዋናዎቹን ዓለም አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ዓይነት ይዘረዝራሉ፣ | /1 ክፍለ ጊዜ/ | |
| **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት** | | |
| ስለ ባህላዊ ሙዚቃዎች የሚያወሳ መዝሙር የሚያስተላልፈውን ፍሬ ሐሳብ ያስረዳሉ፣ | 7.4 ዓለም አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት፣<br>▪ የጃዝ ከበሮ ዘመናዊ ከበሮዎች ወዘተ… /1 ክፍለ ጊዜ/<br><br>7.5 መዝሙር እኛም አለን ሙዚቃ /2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ ዓለም አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ ጥያቄ ማቅረብ፣<br>▪ የአለም አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ሥዕሎች<br>▪ ዓለም አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ሞዴል ሥዕል በማሳየት አይነታቸውን ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ፣<br>▪ ለመዝሙሩ ተስማሚ የሆነው መዝሙር የማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የክልሉን የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች አይነትና አጠቃቀም መለየታቸውን ማረጋገጥ፣
- ሀገር አቀፍ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣
- ዋና ዋና ዓለም አቀፍ ሙዚቃ መሣሪያዎችን መዘርዘራቸውን ማረጋገጥ፣
- እኛም አለን የተባለውን ዘፈን/መዝሙር/ መዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-**

- ቴፕሪከደር የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች፣ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ሞዴሎች ሥዕሎች ወዘተ…
- መዝሙሩ የተቀረጸበት ካሴት፣